## ክፍል ሁለት

# በወያኔ/ ኢህአዴግ ማልያ

በክፍል አንድ ጽሁፋችን በወያኔ ኢህአዴግ ማልያ የህዝብ ተወካይነት ምን ማለት እንደሆነ፤ በአገር ሉአላዊነት ላይ፤ በዜጎች ሰላማና አብሮ የመኖር ጉዳይ በደረሱ በሚደርሱ ጥፋቶች፡፡ በገባንባቸው ጦርነቶች ለአለቁ ለተጎዱ ዜጎች። የሰራዊቱ አባላት። ለሚራበው ዜጋ፤ በአጠቃላይ አገሪቷ ላለችበት የዛሬ ችግር ውሳኔው ላይ የይስሙላ ድርሻ ቢኖራችሁም ከህግ አኳያ በምትጋሩት እኩል የሀላፊነት ድርሻ ሊያስከትልባችሁ የሚችለውን አደጋ ለማሳየት ሞክረናል።

ለአለፉት አስራ ስምንት አመታት የማንኛውም ውሳኔ ምንጭ የወያኔ ክብ ውስጥ ከአሉት በይበልጥም የመለስ እንደሆነ ለማንኛችንም ምንም መከራከርያ ልናቀርብበት የማይችለን ንጹህ እውነት ነው። ለተሰሩ ስህተቶችም ሆነ ጥፋቶች ዋናው ምክንያት የአንድ ሰው ጭንቅላት ብቻ ለአስራ ስምንት አመታት ስራ ላይ መዋሉ ነው። ለዛውም ምንም አይነት የአገርና የህዝብ ፍቅር የሌለው ግለሰብ።

የህዝብ መወሰኛው ምክር ቤትን አይነት ከአንድ ሰው ጭንቅላት በላይ ስራ ላይ እንዲውል እድልን የሚሰጥ ድርጅት በኢትዮጵያ ላይ በህግ ሲቋቋም ግልጽ የሆነው የተሰጣችሁን ሀይል በአግባቡ ተጠቀማችሁም አልተጠቀማችሁም በነዙህ አየነት የመንግስት አደረጃጀቶች ውስጥ በመሳተፍ ድርሻ እስካላችሁ ከህግ አኳያ አብሮት የሚመጣውን ተጠያቂነት እኩል እንድትጋሩ ነው።

እናንተንም ጨምሮ ሁላችንን ተጎጂ የሚያደርጉ ከፍተኛ የሆኑ ጥፋቶች በአገርና ህዝብ ላይ ለአለፉት አስራ ስምንት አመታት ተፈጽመዋል። እነዚህ ጥፋቶች እስከሞት ፍርድ የሚያደርሱ የአገር ክህደት፤ የዘር ማጥፋት፤ በመሳሰሉ ከባባድ ወንጀሎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

ያ የምጸአት ቀን እንደሚመጣ ሁሉም በርገጠኝነት ያውቀዋል። የማይቀርም ነው። ማምለጫ የመሰላቸውን መንገድ እየሰሩ ከአሉት የወያኔ ቁንጮዎች ጀምሮ በዚህ ስረአት ውስጥ የተነካካ ሁሉ ይህ ጉዳይ ብቻቸውን ሲሆን ተኝተውም የሚቃዡበት ነው። ለዚህ ማረጋጋጫው ሲያቦካ ከርሞ ከአገር የሚወጣው፤ መሸሻውን እያዘጋጀ ያለው ቁጥሩ ብዙ መሆኑን ነው መረጃዎች የሚያሳዩት።

መለስና (ክቡ) ውስጥ ያሉ ትክክለኛ በመሆን ከህዝብ ወገን ሊያደርጋችሁ ይችል የነበረ ውሳኔያችሁን። አገርና ህዝብ ላይ የደረሰውን ጥፋት ለማስቀረት እናንተንም ከከፋ ወንጀል ከተጠያቂነትም ሊያድናችሁ ይችል የነበረውን ነጻ አይምሯችሁን ተጠቅማችሁ በኢትዮጵያዊነት ልትሰጡ ትችሉ የነበረውን ድምጻችሁን። ጉዳትና ጥቅሙን አመዛዝናችሁ ልትሰጡ ትችሉ የነበረ ፍርድን ለአንዴም እንዲኖራችሁ አልፈቀዱም። እናንተም መብት አድርጋችሁ አላያችሁትም ምንም አይነት ጥረትም አላደረጋችሁም።

ጥፋት አልጠፋም ወይ ጥፋት መሆኑን አውቄ ተቃውሜ ነበር ልትሉ አትችሉም። በተወሰነ ደረጃ አድርጋችሁትም ሆኖ ቢሆን ነገ ነጻ በሚያደርጋችሁ ሁኔታ ማስረጃ ልታቀርቡበት አትችሉም። ብትሞክሩም በዛን ሰአት ሰሚ አያገኝም።

ግን ለምን እነመለስ ውሳኔዎች የነሱ ብቻ እንዲሆን እርግጠኛ ከአደረጉ በኋላ ለዚህም ማድረግ የሚገባቸውን ሰራ ሁሉ ሰርተው ተጠያቂነቱን ግን እንድትጋሯቸው አርገው አዘጋጁት?። ይህም ብቻ አይደለም ትንሽ ጊዜን ለነሱ ይገዛል ብለው ስላሰቡ ብቻ ነገ መፈረጃችሁ የሚሆነውንም ህግ አሰርተዋችኋል።

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በወያኔ ማልያ የህዝብ ተወካይ የሆናችሁ በአጠቃላይ የመለስ ተከፋይ የሆነ ሁሉ አንድ አይነት የተሳሳተ የአስተሳሰብ ብዥታ ውስጥ ያላችሁ ይመስላል።

“እኛም ነጻ አልነበርንም። ለጠፋው ጥፋት ሁሉ ከመነሻው የሂደቱ አካል እንድንሆን ሲደረግ ጀምሮ ጥፋቶቹ ላይ በነበረን ድርሻ አስገዳጅ የሆኑ ተጽኖዎች ነበሩብን። ይህን ሁሉም ስለሚያውቅ እነመለስን እንጂ መጪዊው ጊዜ እኛን ተጠያቂ አያደርገንም ብሎ ማሰብ“። በርግጥ ተጽኖ ነበረባችሁ። ይህ በኋላ ላይ ለመጸሀፍ ፍጆታ ይውል እንደው እንጂ በፍጹም ከተጠያቂነት ሊያድናችሁ ግን አይችልም። በተፈለገው ሰአት አድማጭ አግኝቶ ሊረዳችሁ መቻሉም አጠራጣሪ ነው።

ለዚህ የተሳሳተ አስተሳሰባችሁ ምን አልባት መበረታታን የፈጠረው በህዝብ ዘንድ አሁን በብዛት የሚታየው ወደኋላ ከመወነጃጀል ለአንዴ እንኳ ያለፈን ትተን ወደፊት እንይ አይነት አስተሳሰብ። ተቃዋሚው ደጋግሞ የሚጠይቀው አገራቀፋዊ እርቅ። ብዛታችሁ። በተወሰነ ደረጃ በነመለስ መተማመን በይበልጥም በግልጽ በሚታየው ከአደጉ አገራት ባንዳ ስለሆነ ለመለስ የሚቸረው ድጋፍ ስረአቱን እድሜ እንዲኖረው ይረዳል ብሎ ማሰብ። የተሰሩ ህንጻዎችና መሳለጫ መንገዶች ግምት ውስጥ ይገባሉ። የመሳሰሉት ምክንያቶች እንደሚሆኑ መገመት ይቻላል።

እነዝህ ሁሉ ሁኔታዎች መጪዊው እድላችሁ ላይ ድርሻ አይኖራቸውም ብለን መከራከር አንፈልግም። ከምክንያቶቹ የበዙት ለመንግስቱ ሰዎች እንደነበሩና እንዳልሰሩ ግን አይተናል። አሁን የጠፋውን ጥፋት ክብደት፤ በአንጻራዊ የተጎዳውን ህዝብ ብዛት፤ የምሬቱን ደረጃ ግምት ውስት ስናስገባ። አሁን አርቀ አሳቢ፤ ሚዛናዊ የሚመስለውም ዜጋም ሆነ የውጪውም ድጋፍ ከሁኔታዎች ጋር እንዴት ሊቀየር እንደሚችል ስለምናውቅ እ.ም.ም ምክንያቶቻችሁ በምጸአት ቀን አዘናጊ ከመሆን ያለፈ በፍጹም አዳኝ የሚሆን አይመስለንም።

በመጀመርያ ዛሬ ከጽንፈኞቹ ውስጥ ነን። አሁን እየሄዳችሁበት እንዳለው ለነጻነታችን እንቅፋት የምትሆኑ ከሆነ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እያንዳንዳችሁ ተሰቅላችሁ አገርና ህዝብን መታደግን ከሚመርጡት ውስጥ ነን። ይህ ዛሬ ነው። ነገ ጊዜው ሲመጣ ግን ዛሬ ጽንፈኛ ያደረገን ምክንያት አግባብ ያለው ፍትህን እንድታገኙ እንድንጠይቅ ወይ ሚዛናዊ ከሚሆኑት ውስጥ እንድንገኝ እንደሚያደርገን እርግጠኞች ነን።

ከመነሻውም ከናንተ ወገን እንዳልሆንን እንደምትገምቱ ብናውቅም። ለአገርም ለናንተም የጠቅም ይሆናል ያልነውን ሀሳብ ልንጠቁማችሁ ስለሆነ ሀሳቡ ክየት የመነጨ እንደሆነ አውቃችሁ ብታነቡን ችግር ያለው አይመስለንም። ከሚቃወሙን ለምን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ቀላል ነው። ከመጠቀም አኳያ ከአልሆነ ከመቶፊዝ አኳያ የማትጎዱበትን የሚጠቁማችሁ የላችሁም። ሀሳባችን ያስፈልጋችኋል። ሌላው ለአለፉት አስራ ስምንት አመታት እነመለስ በአገር ላይ የአደረሱት ጥፋት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ  እንደኢትዮጵያዊነት በጋራ የምንጎዳባቸው ናቸው። ልዩነቱ ድሎተኛ ተጎጂዎች መሆናችሁ ብቻ ነው። ያም ብቻ ሳይሆን ለውጥ እንዲመጣ ሊኖራችሁ የሚችለው ከፍተኛ ድርሻ ወይ ፍላጎት የበዛ እንጂ ከማንም ያነሰ አይደለም ብለን ስላመንንም ነው።

የአይምሮ ነጻነት የሚሰጣችሁን ትክክለኛ እርምጃ ለአንዴ እንኳ ማድረግ የምትፈልጉ ከሆነ እራሳችሁን ለነጻነት የሚደረገው እንቅስቃሴ በአንድ ወይ ብሌላ መንገድ አካል አድርጉ። መዳኛውም መንገድ ይህ ብቻ ነው። በርግጠኝነት በኋላ ከመፈረድ ወይ ተጠያቂነትን ያቀላል። የውስጥ አርበኛ አርገው እራሳቸውን ያስመዘገቡ መቼም ቢሆን ወደኋላ ሄደን የኛንም የሌሎች አገሮችን ታሪክ ስናይ እራሳቸውን ማትረፍ ችለዋል። አሁን በአለው የአገራችን ሁኔታ የመለስ ተከፋይ አገልጋይ ለሆነው ሁሉ አሁን የሚታየው መውጫ አንድ መንገድ ይህ ነው። በይበልጥም መሳርያ ለአልያዘው ክፍል።

## ማድረግ ያለባችሁ።

1.በትግሉ ውስጥ ልናበረክት የምንችለው ድርሻ ይኖራል ብላችሁ እመኑ። ከታጋዩ ክፍል አስተዋጸ ለማድረግ ያላችሁን ፍላጎት የሚያበረታቱ በመልካም ሊያዩት የሚችሉ ብዙዎች እንደሆኑ አትጠራጠሩ።

2.በአካል ቀርቦ የሚጠይቃችሁ እስኪመጣ አጠብቁ። በዛም መንገድ የሚደርሳቸው እንዳሉና አጋጣሚውን እየተጠቀሙ ያሉ ቢኖሩም ሁላችሁንም ለመድረስ ከደህንነት አኳያ ችግሮች ይኖራሉ። የመጀመርያውን የመገናኘት እርምጃ ውሰዱ። ለዚህ እራሳቸውን አስተማማኝ በሆኑ መገናኛዎች የተዘጋጁ ድርጅቶች አሉ።

በአካል ከሚደረሳችሁ እናንተ ለመገናኘት የመጀመርያውን እርምጃ መውሰዳችሁ ከደህንነት አኳያ ትክክለኛ እርምጃም ነው። ላለመጠለፍ ያለውን እድል ያስቀራል። መውሰድ ያለባችሁ ጥንቃቄ ግን ይህ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ፤- የመስራቤት፤ የግልን የቅርብ ቤተሰብን፤ ኮንፒዩተር የጅ ስልክ ለመገናኛ በፍጹም አትጠቀሙ።

3. አስተዋጹችሁ ሊያስገኝላችሁ የሚችለውን እውቅና በፍጹም ለመጠየቅ ወደኋላ አትበሉ ። በውጪያዊ አካል መታቀፉ አንዱ ጥቅም ትግሉ ላይ ለነበራችሁ አስተዋጸ እውቅናን አስተማማኝ ከሆነ አከል በእጃችሁ የሚያሲዛችሁ ነው። ያም ብቻ ሳይሆን ወሳኝ የሆነ አስተዋጸችሁን የምትጠየቁት ለደህንነታችሁ አስፈላጊው

ጥንቃቄ ተደርጎ ነው። እርምጃው በደንብ ታቅዶበት የሚያመጣው ውጤት እርግጠኛ ሲኮን ነው። ይህንኛው ምርጫ ለደህንነታችሁ የተሻለ አስተማማኝ ነው። በህቡ በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ውስጥ መታቀፍን በብዙ ምክንያቶች እኛም የምንመክረው ነው።

ይህ በውጪያዊ አካል ታቅፋችሁ አስተዋጾ ማድረግ ለምትፈልጉ ነው። ይሄንኛው መንገድ ከአልተመቻችሁ በአላችሁበት ማድረግ የምትችሏቸው ነገሮች አሉ። በየትኛውም ማልያ የህዝብ ተወካይ ስትሆኑ አብሮት የሚመጣ ሀይል አላችሁ። እንደውም ተቃዋሚ ከምትሆኑ በመለስ ማልያ መገኘታችሁ ዋስትናችሁን ያበዛዋል ሀይልን ይሰጣችኋል እንጂ አክብደን እንደምናየው የሚያሳንሳችሁም ለመታገል ጎጂም በፍጹም አይደለም።

መለስ በሱ ማሊያም ይህዝብ ተወካይ ስትሆኑ አደጋ እንዳለው ያውቃል። እያወቀ እየፈራ ሌላ አማራጭ ስለሌው ብቻ ነው። ለፍራቻው የመፍትሄ ብለህት አድርጎ የመረጠው መንገድ ከከበሬታ ጋር አለማወቃችሁን መጠቀም እና እሱ ስለፈቀደ እንጂ እንዳልተመረጣችሁ ለአንዴም እንዳይዘነጋችሁ ማድረግን ነው።

ምን ያህላችሁ ለህዝብ መወሰኛው ምክር ቤት እጬ ሁኑ ስትባሉ ሆነ ቦታውን ከያዛችሁ በኋላስ የያዛችሁት ሀላፊነት ምን ማለት እንደሆነ በትክክል ግንዛቤ ነበራችሁ?። እናንተው መልስ ስጡበት። ከማወቅ ጋር የሚመጣው ይህ ከፍተኛ ስልጣን ሊሰጣችሁ የሚገባው የሀላፊነት ስሜት፤ በራስ መተማመን፤ ሀይልስ አላችሁ?።

ይህ ያልሆነበት በቂ ምክንያት አለው። እዚህ ስልጣን ላይ እራሳችሁን ያገኛችሁበት ሁኔታ እራሱ ብዙ ችግሮች አሉበት። የህዝብ ተወካይ እንደሆናችሁ ሆን ተብሎ ከመረጣችሁም ከአጠቃላይ ህዝብም ትነጠላላችሁ። የአገሪቷን ተጨባጭ ሁኔታ እንዳታውቁ ይደረጋል፤ የተለዩ አማራጮችን ለማየት እድሉ የላችሁም። እንደአውሬ አንድ አካባቢ ተሰብስባችሁ ተዘግቶባችኋል። ማወቅ ከሰማይ አይመጣም። ከወከላችሁት ህዝብ ጋር አትገናኙም። የግል ቢሮ በክልልችሁም አዲስ አበባም የላችሁም። በአመት ወይ በስድስት ወር መለስ ከሚነግራችሁ ውጪ በየእለቱ ከመሁራን ስለአገሪቷ ተጨባጭ ሁኔታ፤ ስላሉ ችግሮች ገለጻ አይደረግልችሁም።

ፖሊሲዎችን፤ ህጎች፤ ደንቦች እናንተ ነበራችሁ ማርቀቅ  የነበረባችሁ። ማን እንኳ እንዳዘጋጀው የማታውቁት ረቂቅ ላይ ደምጽ እንድትሰጡ ትጠየቃላችሁ። ይህ ሁሉ ሆን ተብሎ ነው የተደረገው። ትክክለኛውን መንገድ እነመለስ አጥውት አይደለም። ሂደቱ ማወቅን ያመጣል። ይህ ደግሞ በጣም የሚፈሩት  የማይፈልጉት ነው።

በርግጥ ምክር ቤቱ ውስጥ ብቻ በመቆየትም ማወቅ ይመጣል። ከአዋዋላችሁ ፖለቲካዊ ብስለታችሁም እንደሚያድግ የታወቀ ነው። በታማኝነት ደረጃ የኋላ አስተዋጾችሁ እየታየ ቢሆን አንዳችሁም በሌላ መተካት አልነበረባችሁም። ዲሞክራሳዊ ሂደት ስለሆነ ነው እንደማትሉን እርግጠኞች ነን!!። ፍጹም ታማኝ ነበራችሁ። ግን ስንቶቻችሁ ሁለት ወይ ሶስት ዙር እንድታገለግሉ

ተፈቅዶላችኋል?። ለምሳሌ፤- የጥንታዊ ጦርነት በሚባለው ወገን እንደጉድ ከረገፈበት የኤርትራ ጦርነት በኋላ ባድሜን ለኤርትራ ለመመለስ ድምጻቸውን የሰጡ የምክርቤት አባላት ከታማኝነት አኳያ ነገ የሚያስከትለው ተጠያቂነቱ እንዳለ የመለስን ፍላጎት በመሙላቱ ቢሆን ለዘለአለሙ በወያኔ ማልያ የህዝብ ተመራጭ ኡእሆናችሁ ሁሉ በሆናችሁ ነበር?።

እሱም እናንተም ነጻ በሆነ ምርጫ አልተመረጣችሁም። ስለእውነት ከአየነው ሁላችሁም ህዝብን እንዳማትወክሉ ግልጽ ነው። ነጻ ምርጫ አለመኖሩ ግን እራሱንም እናንተንም ወደ ስልጣን ከማምጣቱ በበለጠ እናንተን በፈለገው መንገድ ለመጠቀም ከምንም በላይ ለመለስ አገልግሎታል። በአለመወከላችሁ ምክንያት የሚመጣውን በራስ አለመተማመን በአግባቡ ተጠቅሞበታል።

ከላይ እንዳልነው ሁለችሁም በአግባቡ ህዝብ አልወከላችሁም። ቁም ነገሩ ያለው ግን እዚህ ላይ ብቻ አይደለም። እሱ በአግባቡ ያልተወከለ መሆኑ ሳይዘው እናንተን እንዳሻው ለመጠቀም ድፍረቱን ሲሰጠው። እናንተን ግን ለአንዴ እንኳ የያዛችሁት ከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ሊሰጣችሁ የሚገባው ሀይል እንዳይሰማችሁ በማድረግ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ ለአስራ ስምንት አመት በደንብ ችሏል።

አንድ ጥያቄ እናንሳ እስቲ። ለምን ይመስላችኋል መለስ በምክር ቤት ውስጥ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እንኳ ለማስመሰል በኢህአዲግ ማልያ የተለየ ሀሳብን ለአንዴ እንኳ እንዳይኖር ለአስራ ስምንት አመት እርግጠኛ ያደረገው፡።

በምክር ቤት ውስጥ መለስተኛ ተቃዋሚ መኖር እንዳለበት ሲያውቅ በኢህአዲግ ውስጥ ይህን አይነት አካሄድ ለፖለቲካው ውበት እንደሚሰጥ ጠፍቶት ነው?። በፍጹም አይደለም። በአለም ላይ ከነበሩ አንባገነኖች በተለየ ዲሞክራቲክ መስሎ ለመታየት እንደሚጥር ሁላችንም እናውቃለን። ይህን አይነት ሙከራ ግን አስተማሪ ስለሆነ የሚያመጣውን አደጋ ድራሹን እንደሚያጠፋው ያውቃል። እባብ አይደል በደንብ አስቦበት አስልቶ ነው።

ደግሞም ማድረግም አለበት። በአግባቡ አልተጠቀማችሁም እንጂ እያንዳንዳችሁ በምንም መንገድ ስልጣኑን ያዙት። የህዝብ ተወካይ ስትሆኑ ያላችሁ ሀይል ከፍታኛም አደገኛም አስፈሪም ነው። በጋራ ሀይላችሁ ሲገለጽ በአንድ አገር ላይ ምንም ማድረግ ይችላሉ ወንዱን ሴት ነው እስከማለት ተብሎ ነው። በግልም በአሁኗ ኢትዮጵያ ከአንድ ምክር ቤት አልገባህም ከተባለ ተቃዋሚ መሪ የተሻለ ደህንነትም የለውጥ ሀይል መሆንም፤ ተሰሚነትንም መፈጠር ትችላላችሁ።

ሁላችሁ በአንድ ድምጽ አብራችሁ ብቅ ማለት ብትችሉ እሰየው። የግድ ይህ መሆን ግን የለበትም። በኢህአዲግ ማልያ የህዝብ ተወካይ የሆናችሁ መለስተኛ ቁጥርም ቢኖራችሁ የጋራ የሆነ የራሳችሁ ድምጽ ይዛችሁ ብቅ ማለትም በደንብ ትችላላችሁ። ። የሚፈልገው የአንድ ጊዜ ድፍረትን የሚጠይቅ ለነጻነት መወሰድ ያለብት የተባበረ ህዝባዊ ውሳኔን ነው።

ታሪክን ለመስራት ሁላችንም እኩል የሆነ ሀይል፤ አጋጣሚም፤ ድርሻም አለን

የምንለው ለዚህ ነው። ለውጥን መፈለግ ላይ እና ለነጻነታችን ማድረግ የምንችለውን ዘርፌ ብዙ መንገድ ስናይ የተደገመብን ነው የሚመስለው። ለነጻነታችን ያለንን ቀኖዊነት፤ ለለውጥ ያለንን ፍላጎት ሲታይ እኛ ህዝብ ነን። እኛ ሰማኒያ ሚሊዮን ነን ብለን እራሳችንን መግለጽ ያስችለናል።

የሚፈልገው አሁንም እንደግመዋለን ሁሉ እንዳለበት ሁኔታ ሊያደርገው የሚገባ የተጠና አንድ ድፍረት ያለበት እርምጃ ነው። በሺ መንገድ ሊመጣ የሚችልን ነገር በጃችን ላይ አስቀምጠን እንደመና ከሰማይ እንዲወርድ ስንጠብቅ፤ ስንጠባበቅ ሁላችንም ይዘቱ ይለያይ እንጂ በጭቆና ስር እየኖርን ነው።

ይህን አይነቱ እርምጃ ውሳኔን ይፈልጋል ጥንቃቄ ያለበት የማስተባበር ስራ ያስፈልገዋል። በኋላ የምንመጣበት ቢሆንም ሊያስከትልባችሁ የሚችለው አደጋ ግን መለስተኛ ነው። ተሳክቶላችሁ ይህን አይነት እርምጃ መውሰድ የቻላችሁ ቀን ግን ሶስት መቶ ስልሳ ድግሪ ነው ፖለቲካውን የምታዞሩት። እመኑን ከእውቀት ማነስ፤ የማይቻል መስሎት፤ ፈርቶ ግራ የተጋባውን ሁሉ አንድ የዚህ አይነት እርምጃ ማወቅን መደፋፈርን ስለሚያጨር በርግጠኛነት የበዛውን የምክርቤት አባል ከጎናችሁ ነው የሚያደርገው። ይህም ብቻ አይደለም ጠንክራችሁ ከሰራችሁና ከገፋችሁበት ነጻ የሚያደርገንን የለውጥ ሂደት ለመምራትም ለማካሄድም ከማንም ያነሰ እድልም አይደለም ያላችሁ። በሂደቱ እራሳችሁን ከማይቀረው ከከፋ ችግርም ትታደጋላችሁ።

## <u>ያሉ አጋዥ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው</u>

-በትክክለኛው መንገድ ናችሁ አይደላችሁም ሌላ ጥያቄ ነው። የህዝብ ተመራጮች ናችሁ። የኢትዮጵያም ህግ፤ አለምም የሚያውቃችሁ በዚህ ከፍተኛ የመንግስት ሀላፊነት ቦታ ላይ ለዛውም ህዝብን ወክላችሁ እንዳላችሁ ነው።

-የህዝብ ተመራጭነታችሁ በወያኔ/ ኢህአዴግ ማልያ ነው። አጢነን ከአየነው ሊኖረው የሚችለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። የሚያመጣው የራሱ ከፍተኛ ፖለቲካል ሀይል ተጽኖም አለ።

-የመለስን ማልያ ስለለበሳችሁ መለስን ለመቃወም አይደለም ከመነሻው እናዳይመረጥ ለማድረግ። ከተመረጠም በኋላ እንዲወርድ ለመጠየቅ የያዛችሁት ቦታ ከህግ አኳያ ይፈቅዳል። ድምጻችሁን ልትነፍጉት መብታችሁ ነው። የተወካዮች ምክር ቤት አባል ስትሆኑ በማንኛውም ድምጻችሁን በሚፈልግ ጉዳይ ላይ ቢቻል የህዝብን ፍላጎት እንድታነጸባርቁበት ያም በአይሆን ትክክል ያላችሁትን የራሳችሁን ሀሳብ ስራ ላይ እንዲውል ተጽኖ እንድታደርጉበት ነው።

-ከፍተኛ የሆነ መከታ ሊሆን የሚችል የህዝብ ድጋፍን ያስገኛል። ተቃዋሚውን ከጎናችሁ ያሰልፋል። ከናንተ ጋር ቢሆንም ቀድሞ ትግሉ ውስጥ የታቀፈው የሀይል ሚዛን እስኪስተካከል መጠበቁን ትቶ ከጎናችሁ ይቆማል።

-ለስልጣን ይጠቅማል ተብሎ በዘር ተከፋፍላችሁ ነው የተሰራችሁት። አንድ አይነት

የለውጥ እርምጃ ለመውሰድ ይህ አደርረጃጀት እንቅፋት ተደርጎ በታጋዩ ዘንድ በተለምዶ ይወሰዳል። የቅርብ ጊዜው ምርጫ 97 እንኳ የሚያስተምረን ግን ይህን አይደለም። ቀላል ሎጂክ ነው። የፈለገ ተከፋፍሎ ቢሰራ የተበደለ ያብራል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ አስፈሪ አድሏዊነት ግጥም አድርጎ ነው ያለው። ለብዙሀኑ መብትን በማጣት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዘር እየተለቀመ የሂወት ዋጋን በሚያስከፍል አስፈሪ በሆነ ደረጃ። ከትግራይ ያልሆነው ዜጋ ሁሉ እያመመው ነው የሚኖረው። በዘር እየተቆመረ አድሏዊነት በዚህ ደረጃ ሲኖር ሰው ለሆነ ፍጡር ፍላጎት ለራስ በማግኘት ብቻ በፍጹም አይቆምም። የመጀመርያውን ድፍረት ያለበት እርምጃ ለምትወስዱ ተቃውሚችሁ ይፋ እስኪሆን ነው እንጂ ከጎንችሁ የሚሰለፈው ቁጥሩ እመኑን ብዙ ነው።

- የህዝብ ተወካይ በመሆን በምታገለግሉበት የጊዜ ገደብ ያለመከሰስ የህግ ከለላ አላችሁ። ይህን ከፍተኛ መብት አታሳንሱት። ይህን መብት የሚያሳጣችሁ መልሶ አብላጫ ቁጥር ያለው የራሳችሁ የህዝብ ተወካዮች ድምጽ መሆኑንም አትርሱት።

- አይምሮችሁን ክፍት ካደረጋችሁና ለመማር መለስተኛ ጥረት ከአደረጋችሁ የዓለምንም የአገራችንን ፖለቲካ፤ አገሪቷ እየሄደችበት ያለውን ችግር ለመመርመር የተሻለ ቦታ ነው ያላችሁት።

- መስራት ያሰባችሁትን ለመፈጸም የተሻለ ጊዜም፤መገናኘትም የገንዘብ አቅምም አላችሁ።

መውሰድ ያለባችሁን ጥንቃቄ ላይ ከማውራታችን በፊት የአለባችሁን ተጽኖ ሊገጥማችሁ የሚችለው ችግር በዛሬይቱ ኢትዮጳያ ዜጋው ሰርቶ በሰላም ለመኖር ከሚገጥሙት ችግሮች አኳያ በአንጻራዊ ብታዩት ጥሩ ነው። ለአለፉት አስራ ስምንት አመታት ህዝብ ያልኖረውን ችግር፤ ህዝብ ያልከፈለውን መሰዋትነት እናንተ ላይ ተለይቶ የማትወጡት አይነት የተለየ ተአምር አይመጣም።

በመጀመርያ ምንም አይነት መሰዋትነትን ማስቀረት ወይ መቀነስ ይቻላል። የወያኔ ክቡ ከወሰዳቸው ጥቃቶች ሁሉ የምንማረው። ማድረግ የሚገባን ጥንቃቄ ከአለመውሰድ። ቀድሞ ዝግጅት ከአለማድረግ። ብለጥ ከአለመሆን። ወሳኝ ሁኔታ ላይ ደርሶ ከመዝረጥረጥ ወይ ከመቅደም ነው መጎዳት የመጣው።

ከደህንነት አኳያ ከማንም በተሻለ ሁኔታ ውስጥ ሆናችሁ ነው የምትታገሉት። ከቡ የፈለገውን እርምጃ ልውሰድ ቢልም ፍጹም ምቹ በአልሆነ ዋጋን በሚያስከፍለው ሁኔታ ውስጥ ነው የምታስቀምጡት። የሚያስነሳው ከባድ ቀውስ፤ የሚያስገኝላችሁን ድጋፍ በፍጹም አሳንሶ መታየት የለበትም። ይህን በታሳቢነት ይዘን ሊያደርግ የሚችለው ምንድን ነው። መግደልን ከምርጫው እናውጣው። ሰብስቦ ማሰር አይሞክርም አንልም ግን በፍጹም አይችልም። ሊወስድ የሚችለው እርምጃ ከተመረጣችሁበት አካባቢ አስገድዶም ሆነ ፈብርኮ ፊርማ አሰባስቦ የህዝብ

ተወካይነታችሁን መቀማት ወይ ለሚቀጥለው ምርጫ እጩ እንዳትሆኑ መከልከል ነው።

ጥቃቶቹ ከላይ እንዳልነው ማድረግ የሚገባችሁን ከአለማድረግ። ከጥንቃቄ ጉድለት የሚመጡ ናቸው። እርምጃችሁ ወሳኝ ከአልሆነና ስትድበሰበሱ ከቀደማችሁ ብቻ ነው።

ጥቃቱን ለመሰንዘር ቁጥራችሁ ከፍተኛ ተጽኖ አለው። ስንታችሁን?። አንዴ ልዩነታችሁን ተቃውሟችሁን አገር ውስጥ ለህዝብ፣ ለአለምም ይፋ ከአደረጋችሁ በኋላ ይበልጥ ከባድ ነው የሚሆነው። መቃወም ከህግም አኳያ መብታችሁ ነው።

የሀይል ሚዛኑ ለውጥ ማምጣት በአይችል እንኳ እየጠላው ከተቃዋሚ ጋር መኖር ግድ እንዳለ እስከሚቀጥለው ምርጫ መታገስ አለበት። ይህ ደግሞ የጀመራችሁትን ለመጨረስ የአመታት ጊዜ ይሰጣችኋል። ይህም ብቻ አይደለም ለቀጣዩ ምርጫ በህዝብ ዘንድ ከሚያሰጣችሁ ፍቅር አኳያ ቀላል አይደለም። ብርቱካን እንዳትመረጥ ለማድረግ መስራት ያለበትን ያህል ለእያንዳዳችሁ መስራት ሊኖረበት ነው። ፍርማ ማሰባሰቡም ቀላል አይሆንም።

በዚህ ውጣውረድ ውስጥ ማለፉ ቀላል መሰዋትነት ነው አንልም። ነገር ግን ከባድ መሰዋትነት የሚባልም አይደለም። እውነት እንነጋገር ከተባለ በመለስ ማልያ የህዝብ አገልጋይ በመሆን ከወንጀል ላይ ወንጀል በመደረብ ወደፊት ሊያገኛችሁ ከሚችለው አደጋ ብልጥ የሆነ በምንም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሊወስደው የሚገባ ትክክለኛ ምርጫም ነው።

ይህን የምንለው ሲጀመር በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ እንደኢትዮጵያዊነት መገኘታችን እራሱ አንጀታችንን እያሳረረው እየቆረቆረን ነው። ይህን አይነት አጣብቂኝ ውስጥ አንድ ዜጋ መገኘቱን ከልባችን በመጸየፍም ነው።

አንድም በአንጻራዊነት እያየነው ነው። ከናንተ በከፋ ሁኔታ ውስጥ ኖረው የተቃዋሚነት ስራ የሚሰሩ አሉ። አርባ አይነት የክስ ታርጋ ተለጥፎባቸውም ህዝብ የማወቅ መብት አለው ብለው ጀግና የሚያሰኝ የጋዜጠኝነትን ስራ የሚሰሩትን እንይ ። እንደሚገደሉ እያወቁ እርምጃቸው የሚያመጣው መሰረታዊ ለውጥ ውስን በሆነበት ሁኔታም እንኳ በአደባባይ ተቃውመው የሞቱም ወደፊትም የሚሞቱ እንዳሉ ሁላችንም እናውቃለን። ለነጻነቱ ከመራቡ ብዛት ገድሎ ለመሞት የቆረጠው ቁጥሩ እየበዛ ነው። ሌላው አገርና ህዝብን ከነዚህ ዘረኞች ለመታደግ ለራስም ነጻነት ሊከፈል የሚገባ መሰዋትነት አድርገንም ስለምናየውም ነው።

## መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ

1.እርምጃውን ለመውሰድ ቢቻል ቁጥራችሁ ተደማጭ እስኪሆን እንጂ በፍጹም በውስጥ ለውስጥ ስራ ሁሉንም ለማሳመን አትሞክሩ። አንድም ሁለትም ሆናችሁ ጀምሩት ሌሎችን ለማስተባበር ቀጥታ ጉዳዩን አታንሱ። ሀሳቡ ከነሱ በኩል እንዲመጣ ምቾትን ስጧቸው። መቶ በርሰንት እስክትተማመኑባቸው ግን ዝርዝር

ሀሳባችሁን አታካፍሏቸው።

2.አመቺ ግዜና ሁኔታዎችን አጥኑ።

3.ከተቻለ የምትወስዱት ውሳኔ መለስና ግብራበሮቹን ሊገታ የሚችል መሆን አለበት። ያም ከአልሆነ የምታነሱት ጥያቄ ግልጽ አጭር ድግግሞሽ ያለው ይሁን። ሌሎችንም ከጎናችሁ ሊያሳትፍ የሚችል መልክት የያዘ መሆኑን አረጋግጡ።

4. አንዴ ዝግጁ ነን ብላችሁ ከአሰባችሁ በኋላ ተቃውሟችሁን በግልጽ አውጡት። ይህ በፍጹም በፍጹም ችላ ማለት የሌለባችሁ ነው። ለህዝብም ለሜዲያም ለአለምም ይፋ አድርጉት።

5.በክልል ተወካይነት ደረጃ ያለ አደረጃጀታችሁ በመለስ ማልያ እንደመገኘታችሁ በጣም በጣም ጠቃሚ ነው። ይህ የክልል አደረጃጀት በአራት አቅጣጫ ነው ስለት ያለው። ወደጎን አንዳዴ ወደኋላ እየተጠቀምንበት ነው እስካሁን ያለነው። ስልትነቱ ግን ከፍትለፊት ያለው ይበልጣል። ወደፊት በወሰዳችሁት ቁጥር የኋላውና የጎኑ እየዶመዶመ ነው የሚሄደው። እያንዳንዱ ክልል ወደፊት ለማስኬድ ደግሞ ከበቂ በላይ የስካሁኑ ተሞክሮ ምክንያትም አለው። ከዚህ በኋላ ወደፊት ከአልሆነ ወደሌላ አቅጣጫ ማስኬዱ እናንተን ብቻ አይደለም የመጣችሁበትን ህዝብም ተገዢ አይደለም ግልጽ ባርያ እያደረገው ነው።

ጥሩ የህዝብ አመኔታን እያገኙ ከአሉ በአንዱ ድርጅት ውስጥ በሚስጥር አባል በመሆን ወይ በግልም ከሚመስላችሁ የምክር ቤት አባላት ጋር የድርሻችሁን በማበርከት ለነጻነት በሚደረገው እንቅስቃሴ አካል ለመሆን ለሁለቱም ድፍረቱን ከአጣችሁ። አሁንም ሌላ አማራጭ አላችሁ። በርግጥ አገርና ህዝብ ላይ የተደቀነው አደጋ የሚያሳስባችሁ ከሆነ በግላችሁ መጫዊው ሁኔታ እንቅልፍ የሚነሳችሁ ከሆነ። የመንፈስ እረፍትን የሚሰጣችሁን ስራ ለመስራት ብዙ አማራጮች ለናንተም ይኖራል መርምሩ። የተወሰኑትን እናንሳ።

1. ልታሳድሩት የምትችሉት ተጽኖ ውስን ቢሆንም ከአገር ለቃችሁ መውጣት ትችላላችሁ። በህክምናም አሳቡ፤ ለቦታው ብቁ አይደለንም በላችሁ በምልጃም ይሁን በሆነው መንገድ ወደ ሰላማዊው ኑሮዋችሁ ሳይዘገይ ለመመለስ መሞክሩም ሌላ ምርጫ ነው። እዚህ ላይ ቀድማችሁ የወጣችሁት መሰባሰብ እናንተ ከሰራችሁት ስህተት ተምራችሁ ወንድሞቻችሁን መርዳት አለባችሁ። የማስተባበር ስራ መስራት ትችላላችሁ። ዛሬ ሽሽታችሁ በውጪ ስላላችሁ ከተጠያቂነት የመለጣችሁ ይመስላችሁ ይሆናል። የትም ብትሸሹ በአካል መጠየቁም ይኖር ይሆናል። ያም በአይሆን ከጠፋቱ የአገር ሉአላዊነትም እጅግ ብዙ ዜጋ ተጎድቷል። እርቃችሁ ስላላችሁ ሁሉ አማን እንደሆነ ብታስመስሉም ከጸጸትና ከህሊና ወቀሳ አታመልጡም። የጠፋው ጠፍቷል ወደፊት ለማስተካከል ድርሻ ሲኖራችሁ ብቻ ነው እረፍትን የምታገኙት።

2.መጨረሻው ሰአት ላይ ለመሳፈርና እድልን ለመሞከር አትስነፉ። ቢዘገይም ትክክል ከሆነው ጋር ለመቆምም ቢሆን አይምሮችሁን ክፍት አድርጉ። የትግሉን

አካሄድ፤ የፖለቲካውን ሁኔታ በቅርብ መርምሩ አጢኑ። ለሚፈጠሩ ድንገተኛ ሁኔታዎች ዝግጁ ሁኑ።

3. ለጥቃቅን ነገሮች ትኩረት ስጡ። በርግጠኝነት በአካባቢያችሁ ብዙ ነገር ይካሄዳል። የመንግስቱ ሰዎች በአካባቢያቸው እየሆነ ላለው ነገር የበዙት እስከመጨረሻው ሰአት ደንቆሮዎች ነበሩ። ያንቀላፉት የከፈሉበትን ዋጋ ታውቃላችሁ።

4. በውሸት ስም የመረጃ ትንሽ የለውም መረጃን በማሾለክ ድርሻን ልታደርጉ ትችላላችሁ። ማሰብን ከጨመራችሁበት ከቅርበት አኳያ ትግሉ የሚጠቀምበት ቀዳዳ የትሻለ ይታያችኋል። መንገዱን መጠቆም ትችላላችሁ።

5.በገንዘብ ትግሉን መርዳት ትችላላችሁ።

6. ለመለስ መግደል ማሰር ማስፈራራት ትልቅ ሀይሉ ነው። ነገር ግን የሚሰበስባቸውን ሰዎች መምረጥ ላይ ያለው ችሎታ ሌላኛው ትልቁ ሀይሉ ነው። የጨለመባቸውን በግል እያሳሳቃችሁ ጫወታ መሀል እያስገባችሁ የማሳወቅ የማንቃት ስራ መስራት ትችላላችሁ። ሰዎችን ትክክል ነው ብለው ከሚያስቡት ከለመዱት መንገድ ውጪ ሌላም መንገድ እንዳለ ለማሳየት፤ ሀይል እንዲሰማቸው ለማድረግ ብዙ አይነት መንገዶች ይኖራሉ። በዚህ አስተዋጾ ማድረግ ይቻላል። ይህ ለጊዜው እኛ የታየን ነው። ጭንቅላታችሁን እዚህ ጉዳይ ላይ ካሳረፋችሁት እርግጠኞች ነን ብዙ አስተዋጾ ልታደርጉበት የምትችሉበት መንገድ ይኖራል።

***<u>መደምደሚያ</u>***

*ግን ለምን መልክታችን አድማጭ ይኖረዋል ብለን አሰብን?።*

*ለዚህ ከአንድ በላይ ብዙ ምክንያቶች ይኖሩናል። ዋንኛው ግን በወያኔ/ኢህአዲግ ውስጥ ያለውን ሀይል በሁለት ከፍለን ማየታችን ነው። የመጀመርያው አስቦበት ሆን ብሎ በአገር ሉአላዊነት ላይ በህዝቦች ደህነት በሰላም መኖር ላይ ጥፋትን የሚፈጽመው ነው። ዜጋውን ገድሎ አስሮ አስፈራርቶ መኖር ለጊዜው ስለቻለ ሁሉ በጁ ሁሉ በቁጥጥሩ ስራ ያለ የሚመስለው ነው። ለዚህ ክፍል የተሻለውን አማራጭ ማሳየቱም፤ ለማስተማር መሞከሩም፤ ህግን መጥቀሱም፤ መለመንም፤ መማለድም ሊለውጠውም፤ ሊገባውም በፍጹም አይችልም። አፍንጫውን ተይዞ በግድ ሊንቆረቆርለት ሲቻል ብቻ ነው ተገዶ የሚውጠው። ለነገሩማ ይህ ክፍል ከብዛቱ አኳያ ሊለፋበትም አይገባም። ለወደፊቱም እንዳይደገም ለማስተማርያነቱም መሆን ያለበት አፍንጫቸውን መያዝ ነው።*

*ሁለተኛው ክፍል የህዝብ መወሰኛው ምክር ቤት አባላትን አይነት የመለስ ተከፋይ አገልጋዩ የሆነው ነው። ቁሳዊ የሆነውን ጥቅማጥቅም እንደታዛዥነቱ እነደያዘው የሀለፊነት ደረጃ ያገኛል። ከምቾት አኳያ የሚቸግረው ነገር ላይኖር ይችላል። ነገር ግን ነጻ አይደለም። እንደሁላችንም ተጨቋኝ ነው። እንደኢትዮጳያዊነት ተጎጂም ነው። ወደብ አልባ በመሆናችን፤ ለሱዳን በሰጡት መሬታችን፤ ሀዝባችን እየተራበ*

አቅሙ ያላቸው ዜጎቻቸውን እንዲቀልቡ መሬታችን መጨብቸቡ። በኑሮው ውድነት፣ በአድሎው፣ እያልን ብንዘረዝረው እናቁመው እንጂ ማለቂም የለውም።

ከነጻነት አኳያም ስራው መወሰን የሆነው ወስን ሲባል ይወስናል ተቃወም ሲባል ደግሞ ይቃወማል። በአጭሩ ይህ ከፍተኛ ሀላፊነት በትእዛዝ እጅ ወደማውጣትና ወደ ማውረድ ተቀይሯል። በተመሳሳይ ስራው የህዝብን ደህንነት መጠበቅ የሆነው። ግደል የተባለውን አለመግደል አይችልም። ግደል ሳይባልም ደግሞ መግደል አይችልም።

የህዝብ ተወካይነትን አይነት ከፍተኛ ሀላፊነት ላይ ያሉትም ከያዙት ከፍተኛ የስልጣን ደረጃ፣ ከተረከቡት የህዝብና የአገር አደራ ጋር መምጣት ይገባ የነበረው ሀይልና ተደማጭነት በራስ መተማመን ፍጹም እንደተከለከሉ በተለያየ ምክንያት ሙሉ በሙሉ አሳልፈው እንደሰጡት ያሳያል። ምንም ነገር በነሱ ቁጥጥር ስር አይደለም። ለአንዴም ይህ ሀይልና ነጻነት ተሰምቷቸው አያውቅም። አብረን ነጻ እንውጣ ያሉ ልጆችን ግደል ስለተባሉ ብቻ ገድለው። ሱማሌ ሄደችሁ ሙቱ ሲባሉ ሄደው የሞቱ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባለት ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

ይህ ክፍል ቁጥሩ ቀላል አይደለም። በዚህ አዋራጅ በሆነ ሁኔታ መኖር ለሁሉም ተመችቶት ነው ማለት አይቻልም። ሰው ለሆነ ሁሉ ያማል። መንገድም ብናመለክታቸው፣ አቅጣጫ ብናሳያቸው፣ መበረታታን ብንሰጣቸውም በፍጹም አይጠቀሙበትም ብሎ ሊከራከረን የሚችል እንደሚኖር እናውቃለን። ከሚታየው ሁኔታ ከርክራቸው ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል።

ነገር ግን ከማውገዝ በአለፈ ችግራቸውን ተረድቶ መፍትሄ ጠቋሚ በሆነ አግባብ በአለው መንገድ ተሰርቶበታል ብሎ መረጃ ማቅረብ የሚችልም ያለ አይመስለንም። ይህም ብቻ ሳይሆን ለማንኛችንም ሰው የሚለው ፍጡር ላይ ያለንን ከበሬታም እንዳያንስብን ያስፈራል። ቁሳዊ የሆነው ጥቅም ስላገኘ ብቻ የሰው ልጅ በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የአይምሮ ሰላሙን ሰጥቶት አሜን ብሎ እንዲኖር ያደርገዋል ብሎ ለማመን ይከበዳል።

በርግጥ ስልጣናና አብሮት የሚመጣ ጥቅማጥቅቅም በአለጌ ነው። አርቆ አሳቢ ክፍት አይምሮ ላላቸው ከአልሆነ ነገ የማይቀረውን ተጠያቂነት ላይ ማሰቡን ያስረሳል ያዘናጋል።

አሁን በአገራችን በደል ሞልቶ እየፈሰሰ ነው። ዜጋው ላይ መገደል መሰቃየት፣ ያላ ህግ መታሰር፣ ከስራ መባረር፣ ልጆችን ማስራብ ....ሲኖርበት አብሮት የሚመጣውን የጥፋተኝነት ስሜት ከአሳፋሪነቱ ጋር ሁሉም ልንኖርበት ግድ ይላል።

ሁሉ አማን ነው ብሎ ማስመሰሉ፣ በአይምሮችን ውስጥ ያለውን ጭሁት ላለማዳመጥ መጣሩም የማይቻልበት ጊዜ ለሁሉም በየሰአቱ ይመጣል። ያኔ ፍረሀት ወይ ጥፋትን ምክንያታዊ ለማድረግ ሰበብ መደርደሩም ፋይዳ ቢስ ይሆናል። በዛን ሰአት አምላካዊም ሆነ አለማዊ ሀይል ምንም የተጎዳ እንደሌለ ከጸጸት ነጻ የሆነ አይምሮን ሊሰጠን አይቻለውም።

መጽናናትን በመጠኑም የአይምሮ ነጻት እንዲሰማን የሚያደርገን የተተበተብንበትን ሰንሰለት ሰብረን፤ ፍረሀታችንን አሸንፈን የምንወስደው ትክክል የሆነ ማስተካከያ እርምጃ ብቻ ነው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ተፈጥረው ወይ ውስጣችን ያለ እውነት አሸንፎ እራሳችንን እዚህ ስሜት ውስጥ አንድ ቀን እናገኘዋለን። በዛን ቀን ለውሳኔያችንም ልንወስድ ለምንችለው እርምጃ ይረዳን ይሆናልና የዚህ አይነቶቹን የተለዩ አማራጮችን የያዙ ሀሳቦች ከጠላትም ይምጡ ከወዳጅ አንጥላ።


ዳኮታ የጥናት መአከል።
Dakotareserch@yahoo.com

January 23, 2010